# በዓለ ሃምሳ (ጰራቅሊጦስ)

ከኤማሁስ ተመልሰው
በኢየሩሳሌም ተቀምጠው
ሲጠብቁ ከልብ ፀንተው፤
የተሰፋው ቃል ዕውን ሆኖ
ወረደ ተከፋፍሎ
በእሳት አምሳል ተመስሎ።
መቼ ሆነና የጉሽ ጠላ
አድሮ ውሎ የሚጣላ፤
ነበረ እንጂ መንፈስ ቅዱስ
ሕይወት ሰጥቶ የሚፈውስ
ኃይልን አድሎ ልብ የሚያድስ።
ጴጥሮስ አትፍራ ተመላለስ
በአንተ ላይ አድሯል መንፈስ ቅዱስ፤
ያለ ታንኳ ተራመድ በባሕሩ
ዓለም ይግባው ምስጢሩ፤
መንፈስ ቅዱስ ሲያበረታ
ሀዘንን አጥፍቶ ሲሆን አለኝታ፤
ፍርሃትን አስወገዶ
ድፍረትን አለማምዶ
በከሃዲዎች ፊት መቆምን አስወድዶ፤
ኃይልን ሲሰጥ ለወገኑ
ቃሉን አጥተው ለመከኑ፤
ጉስቁሉናቸው ሊጠፋ
ሊታደላቸው የጽድቅ ተስፋ
በክርስቶስ ሊታመኑ
ቀለው ላይገኙ ሲመዘኑ
በክርስትናቸው ሊታወቁ
በምግባራቸው ሊደምቁ
ሊቀርላቸው መናቁ
የተሰፋው ቃል ዕውን ሆኖ
ወረደ ተከፋፍሎ
በእሳት አምሳል ተመስሎ
መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሆኖ
የታመመውን ሊፈውሱ
አሮጌውን ሊያድሱ
በትምህርታቸው ሊያንጹ
ጠማማውን ሊገስፁ
በምስጢረ ጥምቀት ሊያከብሩ
ዕውሩን ሊያበሩ
ዓይንን ሊፈጥሩ በግንባሩ
የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ሊናገሩ
በዓለም ዙሪያ ሊመሰክሩ
ተነሱ ሐዋርያት እየዘመሩ
ለስሙ በድንጋይ ሊወገሩ
ስጋቸውን ክደው ለነፍሳቸው ሊያድሩ።
የተሰፋው ቃል ዕውን ሆኖ
ወረደ ተከፋፍሎ
በእሳት አምሳል ተመስሎ
መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሆኖ

ኃይለ መስቀል ተስፋዬ ከለንደን (ግንቦት 1996)

www.ethiopianorthodox.org